በዚህ ዓይነት የሚቀጥል እንጂ የሚወገድ አይሆንም:: ዕልቂትና ጦርነት፣ ስደትና ሥቃዩም ይባባሳሉ እንጂ አይቀንሱም::

አዲስ መንደር ምሥረታ በሚል ፋሽስቱ መንግሥት የሚያካሂደው ኢትዮጵያን ወደባሰ የሥቃይና የመከራ አዘቅት እየጨመረ ያለና የሚጨምርም ነው:: ፀረ-ሕዝብ ዕቅዶችን እየቀፈቀፈ ተግባራዊ ለማድረግ ልምዱ የሆነው ፋሽስታዊው መንግሥት በሕዝቡ የተባበረና የተጠናከረ ትግል እስካልተደመሰሰ ድረስ የፋሽስቱ መንግሥት አዲስ ዕቅዶችና እርምጃዎች ያው የምናውቀውንና ያንገፈገፈንን የመከራ ኑሮ ከማጠናከር ሌላ የሚያመጡት አዲስ ሁኔታ ወይም አዎንታዊ ለውጥ አይኖርም::

በተባበረ ትግል ፋሽስቱን መንግሥት እንደምስስ!

ትግላችን አለጥርጥር ያቸንፋል!!

የ ትውልድ

የ ጎሠፊዩ